IDOS POLICY BRIEF 27/2023

# ለስደተኞች እና ለስደተኛ ተቀባይ ማህበረሰቦች የስራ እድል እና ማህበራዊ ትስስርን ለማሻሻል የቴክኒክና ሙያ ስልጠና (TVET) ያለው ሚና

## በኢትዮጵያ ከተካሄደው የተፅዕኖ ግምገማ (Impact Assessment) የተገኘ ማስረጃ

አቢስ ጌታቸው ፣ ሊሳ ሆክል ፤ ያና ኩንት፤ አብዲራህማን አህመድ፤ አርሚን ቮን ሺለር

## ማጠቃለያ

መንግስታት እና ለጋሽ ተቋማት የሥራ እድሎችን ለመፍጠርና ምርታማነትን ለማሳደግ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና (TVET) ስርዓትን ከፍተኛ ትኩረት ይሰጡታል፡፡ በዋናነት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሥራ ገበያ የሚጠይቀውን ችሎታ ለተመራቂዎች በመስጠት የሥራ እድልና ብቃት ያለው ሠራተኛ ለማግኘት እንደሚያስችል ይጠበቃል። የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ደጋፊዎች ከስራ ተጽእኖው ባሻገር፤ እንደ አካታችነት፣ የጾታ እኩልነት እና ማህበራዊ አንድነት የመሳሰሉ ማህበራዊ ውጤቶችን እንደሚያሻሽልም ተስፋ ያደርጋሉ።

የሥራ ገበያ መኖር የተፈናቀሉ ሕዝቦች ኑሯቸውን (መተዳደሪያቸውን) እንዳያጡ እና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አንድነታቸውን አስጠብቀው እንዲኖሩ በማድረግ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ለረጅም ጊዜ ከቦታ መፈናቀልና ወደቀየ ለመመለስ ያለው እድል እየቀነሰ መሄዱ ተፈናቃዮች በመጀመሪያ በተጠለሉባቸው አገሮች አንድነት ፈጥረው እንዲኖሩ አበረታች ምክንያት ሆኗል። ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ ተጨማሪ ጥቅም ያገኘው በዚህ ረገድ ነው።

ለመሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና (TVET) የታሰበለትን ተስፋዎች ይፈጽማል? በአጠቃላይ፣ በTVET ተፅዕኖ ላይ የተሰሩ አሃዛዊ ማስረጃዎች ውስን እና ብዘውን ጊዜ እርስ በርስ የማይጣጣሙ ናቸው፡፡ ከሥራና ከገቢ አንጻር ሲታይ አነስተኛ አዎንታዊ ውጤት እንዳለ የሚያሳዩ ማስረጃዎች ቢኖሩም ጊዜ ግን ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ብዘውን ጊዜ ተፅዕኖዎች/ለውጦች የሚታዩት ከመካከለኛ እስከ የረዥም ጊዜ ብቻ ሲሆን በአጠቃላይ TVET ፕሮግራም ለረጅም ጊዜ ስራ አጥነት በተሻለ ሁኔታ ይቀርፋሉ፡፡ የማኅበረሰብ ተፅዕኖዎች/ለውጦች ማስረጃዎች በጣም ውስን ሲሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሊያመጣ የሚችለውን የማኅበራዊ ትስስር ተፅእኖ በተመለከተ ትልቅ የእውቀት ክፍተት አለ። ከተመደበለት የገንዘብ መጠን እና በፖሊሲው ውይይት ከሚጠበቀው ከፍተኛ ግምት አንፃር፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እርምጃዎች በራሳቸው ያወጁትን ዓላማ እያሳኩ እንደሆነና፤ ለማሳካት እንዴት አስተዋፅዖ እንደሚያበረክቱ በተሻለ መረዳት አስፈላጊ ነው።

በዚህ የፖሊሲ ምክረ ሃሳብ በጀርመን የልማት ትብብር ድርጅት Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) በኢትዮጵያ ተግባራዊ ያደረገውን ሁሉን አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥናታዊ ውጤት አቅርበናል። በዚህ ፕሮግራም ማህበራዊ ትስስርን ማጎልበት እና የስራ እድሎችን ማሻሻልን ግልጽ ግቦች በማድረግ ስደተኛ ተቀባይ ማህበረሰብ አባላት እና ስደተኞች በጋራ ሰልጥነዋል፡፡

ውጤቶቹ እንደሚያመለክቱት የማኅበራዊ ትስስር ተፅእኖ በብዙ ገፅታዎች ላይ አስደናቂ ቢመስልም የገቢ እና የሥራ ውጤቶቹ ተፅእኖ ግን በጣም ደካማ እና ለተወሰኑ የግለሰቦች እና ቡድኖች ብቻ ነው፡፡ ማህበራዊ ትስስርን ለማግኘት አይነታዊ (qualitative) እና አሃዛዊ ማስረጃዎች የአቀራረቡን ትክክለኛነትን ይደግፋሉ፡፡ ከዲዛይን ወይም አፈጻጸም ችግሮች በላይ፣ የጠንካራ የሥራ ውጤቶች እጦት እንደ የሥራ ገበያ የመሳብ አቅም ውስንነት፣ የሕግ ሥራ ፈቃድ ገደቦች፣ የሥርዓተ-ፆታ መሰናክሎች እና መሰል መዋቅራዊ አውድ ሁኔታዎች እና እንቅፋቶች ይዘወራል።

ከትንታኔው የሚከተሉትን ዋና ምክረ ሃሳቦችን እንወስዳለን፡-

- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፤ ለሥልጠናው አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች መመቻቸታቸውን (የሥራ ገበያ አቅም እና የሕግ ማዕቀፍ መሰናክሎችን ጨምሮ) ለማረጋገጥ በትኩረት የሚሠራ የአውድ ትንተና ያስፈልጋቸዋል። በተለይም የሥራ እድል ላይ የሚያመጡት ተጽእኖዎች ግልጽ ባለመሆናቸው ይህ አይነት አውዳዊ ትንተና በተለየ ሁኔታ ጠቃሚ ነው፡፡
- አካታች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማኅበራዊ ትስስርን ለማሻሻል ውጤታማ መሣሪያ ይመስላል። ነገር ግን፣ የማህበራዊ ትስስር ውጤቶች ለስራ እድል ውጤቶች እንደ “ተጨማሪ” ብቻ ሳይሆን እንደ ዋና ግብ የሚገመቱ ከሆነ፣ ጥያቄው የሚነሳው አማራጭ የፖሊሲ ጣልቃገብነቶች የበለጠ ወጤታማ ከሆኑ ነው። ይህ ጥያቄ በዋናነት የሚነሳው የቅጥር እና የገቢ ውጤቶች ማስረጃዎች አመርቂ ባለመሆናቸው ነው።
- የአካታች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብሮች ተፅእኖን በተመለከተ ያሉትን ማስረጃዎች መሰረታቸውን ማስፋፋት ያስፈልጋል። የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በተፈናቀሉ ዜጎች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ፣ ሊያስከትል የሚችለውን የኅብረተሰብ ተፅእኖ፣ የፆታ ልዩነት ተጽዕኖዎች እና የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የቅጥር እና የገቢ ውጤቶች ላይ ያሉት የእውቀት ክፍተቶች መሞላት አለባቸው።

CC BY 4.0 license

## መግቢያ፡- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ለተፈናቃዮች - ተስፋዎች እና ማስረጃዎች

እኤአ በ2022 መጨረሻ (UNHCR, 2023a) በዓለም ላይ የተፈናቀሉ ሰዎች ቁጥር ከ100 ሚሊዮን በልጧል። አብዛኛዎቹ በአለምአቀፍ ደረጃ የተፈናቀሉ ሰዎች (ስደተኞችን እና ጥገኝነት ጠያቂዎችን ጨምሮ) የሚስተናገዱት በአስቸጋሪ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች እና አንዳንዴም የፖለቲካ አለመረጋጋት በሚታይባቸው ጎረቤት ሀገራት ነው። በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ አብዛኛው የአካባቢው ህዝብ ለኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተጋለጠ እና ብዙውን ጊዜ ከስደተኞቹ ያልተሻለ፤ በሚያሳዝን ሁኔታ አዲስ መጤዎቹን እንደ "ተጨማሪ ሸክም" እና በስራ ገበያ ውስጥ እንደ ተፎካካሪዎች የሚያዩ ናቸው፡፡ ብዙዎች ይህ ሁኔታ እንደ ሥራ ቅጥር፣ የመኖሪያ ቤት እና የማህበራዊ አገልግሎቶች ባሉ ውስን ሀብቶች ላይ ሽምያ ይፈጥራል ብለው ይሰጋሉ።

ብሔራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የፖሊሲ እና የልማት ተዋናዮች ለእነዚህ ተግዳሮቶች እና ስጋቶች ምላሽ የሚሰጡት ያላቸው በጀት በሚፈቅደው መጠን ፤የስደተኞችን ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ውህደት ለማጎልበት ይረዳሉ የተባሉ መርሃ ግብሮችን በማጎልበት ነው። እዚህ ላይ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መርሃግብር ዋነኛ መሣሪያዎች ሆነው ይታያሉ። የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እርምጃዎች ደጋፊዎች የተሳታፊዎችን የሥራ ዕድል ለማሻሻል እና በዚህም የተሻሻሉ የሥራ ገበያ ውጤቶች እና አጠቃላይ ምርታማነት፣ ተወዳዳሪነት እና ኢኮኖሚያዊ ውጤታማነት ለማምጣት ጠቀሜታ እንዳላቸው ይናገራሉ (World Bank, UNESCO & ILO, 2023) ። በተለይም የአለም የስራ ልማት ሪፖርት “World Development Report on Jobs” (World Bank, 2012) በስራ እና በማህበራዊ ትስስር መካከል ያለውን ግንኙነት በግልፅ አጉልቶ ካወጣ በኋላ፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች እንደ አካታችነት፣ የፆታ እኩልነት እና የማህበራዊ ትስስርን የመሳሰሉ ዋና ዋና ማህበራዊ ውጤቶችን ላይ ተጽእኖ ማሳደር እንዳለባቸው በመታመኑ እነዚህን እርምጃዎች ለማበረታታት እና ህጋዊ ለማድረግ አስፈላጊ ሆኗል።


ምንም እንኳን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች በዓለም አቀፍ የልማት አጀንዳዎች ውስጥ አዲስ ትኩረትን ያገኙ ቢሆንም ፤ ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ውስጥ ካለው የመፈናቀል አውድ አንፃር እነዚህ ፕሮግራሞች በሥራ ገበያው ውጤት ረገድ ውጤታማነታቸውን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ወጥነት የላቸውም (e.g., Card, Kluve, & Weber, 2010)። ምንም እንኳን ጥናቶች በመካከለኛና በረዥም ጊዜ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ክህሎትን ከማሳደግ አንጻር አነስተኛ አወንታዊ ተፅእኖ እንዳላቸው የሚያረጋግጡ ቢሆንም፣ ይህ ግን ሁልጊዜ ወደ ሥራ ቅጥርና የኢኮኖሚ ዕድገት እድሎች አይለወጥም። የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብሮች በተለይ በገጠር ያለውን የወጣቶችን ሥራ አጥነት በመቅረፍ እና ሴቶችን በማብቃት የተወሰነ ስኬት አግኝተዋል (Kluve et al., 2019)። የመደበኛ ስራ እድሎች ውስንነት፤ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተመራቂዎች በተለይም ሰፊ ኢመደበኛ ኢኮኖሚ ባለባቸው አገሮች ወደ ስራ እንዳይገቡ ማድረጉን ጥናቶች ያሳያሉ (Stöterau, Kemper, & Ghisletta, 2022)።

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከተለያዩ የኅብረተሰብ ውጤቶች ጋር ያለው ተያያዥነት የማስረጃ መሰረቱ በጣም የተገደበ ሲሆን በተለይ ደግሞ ስደተኞች ካላቸው የማኅበራዊ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ህጋዊ አውዶች ጋር ተዳምሮ ያሉት ማስረጃዎች እጅግ የሳሱ ናቸው። የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በማህበራዊ ትስስር ላይ ያለውን ተጽእኖ እንደ አጠቃላይ ጽንሰ-ሀሳብ የሚመረምር ጥናት አላጋጠመንም። በጋራ ትምህርት እና ስልጠና ወይም የጋራ ስፖርት መስተጋብር እና ግንኙነት በቡድኖች መካከል ያለውን ውጥረት በተሳካ ሁኔታ እንደሚቀንስ የሚያሳዩ በርካታ የምልከታ ጥናቶች (observational studies) እና በጣም ውስን የሆኑ የሙከራ ጥናቶች (experimental studies) አሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ ጥናቶች በአብዛኛው ትኩረት ያደረጉት በስደተኞችና በተቀባይ ማህበረሰብ መካከል ሳይሆን በተለያዩ ብሔሮች መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ነው። እንዲሁም በዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች (Lower Middle Income Countries (LMICs)) ውስጥ ባሉ ፕሮግራሞች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች እጅግ ውሱን ናቸው (Paluck, Green, & Green, 2019)።

# የስደተኞች ፖሊሲ እና አካታች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም በኢትዮጵያ

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከ900,000 በላይ ስደተኞችን ከጎረቤት ሀገራት በመቀበል በአፍሪካ ሶስተኛዋ ነች። በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ ስደተኞች በእድገት ወደኋላ በቀሩ ክልሎች ውስጥ በሚገኙ የስደተኞች መጠለያ ካምፖች ውስጥ ለረጅም ጊዜ ኖረዋል። በ2010 ለኤርትራውያን ስደተኞች ከካምፕ መውጣት የሚስችል ፖሊሲ በመደንገጉ ብዙ ቁጥር ያላቸው ኤርትራውያን ስደተኞች በከተሞች በተለይም በአዲስ አበባ ራሳቸውን ችለው መኖር ችለዋል። (ስእል 1 ይመልከቱ)።

## ምስል ፲፡ የስደተኞች ስታቲስቲክስ እና ዋና የሰፈራ ክልሎች በኢትዮጵያ




The boundaries and names shown and the designations used on this map do not imply official endorsement or acceptance by the United Nations

የተቀመጡት ድንበሮች ፣ ስሞች እና በዚህ ካርታ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት ስያሜዎች የተባበሩት መንግስታትን ኦፊሴላዊ ድጋፍ ወይም ተቀባይነት አያመለክቱም።

**ምንጭ፡** UNHCR, 2023b

እ.ኤ.አ. በ2016 በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀውን የኒውዮርክ የስደተኞች ድንጋጌን ተከትሎ፣ ኢትዮጵያ በውስጧ የሚስተናገዱትን ስደተኞችን በራስ የመተማመን መንፈስን እና የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል በርካታ እርምጃዎችን ወስዳለች። እነዚህ ዘጠኝ ቃል ኪዳኖች የሚባሉት ለስደተኞች የሥራ ፈቃድ መስጠትን፣ ለኤርትራውያን ብቻ የተገደበ የነበረውን ከካምፑ ውጪ የመኖር መብት ፖሊሲ (ማለትም በግምት 10 በመቶው የስደተኞች ቁጥር) ለሌሎችም በማስፋት እና ስደተኞችን ወደ ብሔራዊ አገልግሎት ሥርዓት (እንደ ከፍተኛ ትምህርት) ለማካተት ቃል መግባትን ያጠቃልላል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ በማግኘት ዘላቂ የስደተኞች ውህደትን ለመፍጠር የሚያስችለውን ሁሉን አቀፍ የስደተኞች ምላሽ ማዕቀፍ (Comprehensive Refugee Response Framework (CRRF)) ተግባራዊ ለማድረግ የመሞከሪያ ሀገር ሆናለች። እ.ኤ.አ. በ2019 በርካታ የCRRF ቃልኪዳን (ከእነዚህም መካከል፣ የመስራት መብት እና የመንቀሳቀስ መብት) ወደ ብሄራዊ ህግ ተለውጠዋል። ይሁን እንጂ ስደተኞች እነዚህን መብቶች በምን ሁኔታ እንደ መብታቸው ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ግልጽ አይደለም።

እንደ አብዛኞቹ ዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ያላቸው የአለም አገራት (Lower and Middle Income Countries)፣ ከፍተኛ የስራ አጥነት፣ ውስን ሀብት እና የበጀት ችግር የኢትዮጵያ መንግስትን ካጋጠሙት ቁልፍ ተግዳሮቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው (Brown, Mackie, Dickenson, & Gebre-Egziabher, 2018)። በዚህ ምክንያት የሰብዓዊ እና የልማት አጋሮች CRRFን ለስደተኞች እና ለተቀባይ ማህበረሰቦች ተግባራዊ እንድታደርግ ኢትዮጵያን ደግፈዋል። በጂአይዜድ የተተገበረው የQualifications and Employment Perspective (QEP) ፕሮግራም ስልጠናውን ለተቀባይ ማኅበረሰብም በማዳረስ ኢትዮጵያ ስደተኞችን ወደ ብሄራዊ አገልግሎት መዋቅር ውስጥ ለማካተት ያላትን ቁርጠኝነት በመደግፍ ነው። በኢትዮጵያ የመንግሥት ኮሌጆች ጋር በመተባበር በተለያዩ የሙያ ዘርፎች አካታች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና

ሥልጠና ፕሮግራም ለስደተኞችና አስተናጋጆች በጋራ ይሰጣሉ። ከዚህ ጋር፣ ፕሮግራሙ የተሳታፊዎችን የስራ እድል ለማሻሻል ብቻ ሳይሆን በስደተኛው እና በተቀባዩ ማህበረሰብ መካከል ማኅበራዊ ትስስርን ለማሳደግ እና ለማጠናከር ያለመ ነው። ከኢትዮጵያ የፌዴራል የሠራተኛና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የQEP ፕሮግራም በአዲስ አበባ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በሶማሌ ክልል፣ ቢጋምቤላ እና በትግራይ (በአሁኑ ጊዜ በትግራይ ውስጥ በጦርነቱ ምክንያት ተስተጓጉሏል) በመተግበር ላይ ይገኛል።

## የምርምር ትኩረት እና መሰረታዊ የምርምር ንድፍ

ጥናታችን የሚያተኩረው በአዲስ አበባ እና በአሶሳ በሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች፤ የQEP ፕሮግራም ስልጠና ላይ ነው። በዚህ መሰረት በጥናታችን በዋናነት ኤርትራዊያን ስደተኞች የሚሳተፉበትን በኢትዮጵያ ዋና ከተማ ያለውን የስደተኞች ሁኔታ አይተናል፡፡ በተመሳሳይ ከሱዳን እና ደቡብ ሱዳን የመጡ ስደተኞች የሚገኙበትን ፤ እንዲሁም የካምፕ ፖሊሲ (እንቅስቃሴ ገደብ) ያለበትን የአሶሳ (ቤኒሻንጉል ጉሙዝ) ዐውድ አካትተናል።

### ሣጥን 1፡ ተፅዕኖ ተኮር ተጓዳኝ ምርምር

ይህ ጥናት የተተገበረው በ"ተፅእኖ ተኮር ተጓዳኝ የምርምር ፕሮጀክት" አይነት ነው (Funk, Groß, Leininger, & von Schiller, 2018)። በጀርመን ልማት እና ዘላቂነት ተቋም (German Institute of Development and Sustainability (IDOS)) የተዘጋጀው ይህ ቅፅ በተለይ በምርምር እና በተግባር መካከል ያለውን የረጅም ጊዜ ጠንካራ ትብብርን መሠረት የሚያደርግ ሲሆን ለመማር፣ የቅልቅል ዘዴዎችን ለመጠቀም(mixed approach)፤ እና እውቀትን በጋራ ለመፍጠርን አጽንዖት ይሰጣል። ይህም ለምርምር ጥራት፣ ትልቅ ጥቅም አለው።

በጥናቱ የተካተቱት አምስት የተለያዩ ባቾች (እያንዳንዱ ባች ብዙ የሥልጠና ፕሮግራሞችን ያቀፈ፣እንደ አውቶ ሜካኒክ፣ ምግብ ዝግጅት፣ የልብስ ስፌት እና የጨርቃጨርቅ፣ የሆቴል አስተዳደር) በአዲስ አበባ አካታች ስልጠናዎችን ወስደዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁለት ባች ደግሞ በአሶሳ ተሳትፈዋል። ከ2021 እስከ 2023 ባለው ጊዜ ውስጥ ከስልጠናው ተሳታፊዎች ጋር ከሥልጠናው በፊት፣ በሥልጠናው ወቅት እና ከስልጠናው በኋላ እንዲሁም ስልጠናውን ካልወሰዱት መነጻጸሪያ ቡድን ጋር(Control group) በሦስት የተለያዩ ጊዜያት አይነታዊ እና አሃዛዊ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በዚህ መግለጫ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማለት በኮሌጆች የተሰጡ የሙያና ሙያዊ ያልሆኑ የክህሎት (soft skill) ስልጠናዎች እንዲሁም ለአንዳንድ የስልጠና ተሳታፊዎች በድርጅቶች ውስጥ በድንገማ እንዲሰሩ የተደረጉትንም ይጨምራል።

በአጠቃላይ በአዲስ አበባም ሆነ በአሶሳ የነበሩ የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ለስልጠናው የነበራቸው ግምገማ በጣም አወንታዊ እንደነበር ልብ ሊባል ይገባል። በሁለቱም የስልጠና ማዕከላት እንደ ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች ባሉ ተግባራዊ መገልገያዎች ላይ አንዳንድ ቅሬታዎች ቢኖሩም የማስተማሪያ እና የመማሪያ ስፍራዎች፣ የጋራ ክፍሎች (ስደተኞች እና ተቀባዮች) እንዲሁም በሁለቱም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች ውስጥ ያሉ ሰራተኞች አዎንታዊ ግምገማ ተሰጥቷቸዋል። የስልጠናው ተሳታፊዎችን ተሳታፊ ካልሆኑት (Control group) ጋር በማነፃፀር እነዚህን ውጤቶች የበለጠ ጎላ ለማድረግ እና ስለ ፕሮግራሙ ተፅእኖ የበለጠ ለማወቅ እንችላለን።


## የአካታች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም የሥራና የገቢ ተጽእኖን መገምገም

የአካታች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ቁልፍ ዓላማ የተሳታፊዎቹን የሥራ ዕድል ማሳደግ ነው። በዚህ መሠረት ፕሮግራሙ ለተሳታፊዎች ያስገኘውን የሥራ እና የገቢ ውጤቶችን መርምረናል።

በአጠቃላይ የሥራ እድል ውጤትን የሚደግፉ ማስረጃዎችን አላገኘንም፡፡ ነገር ግን ውጤቶቹ ከቡድን ቡድን ከፍተኛ ልዩነት ያሳያሉ፡፡ ለተወሰኑ ቡድኖች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍ የመሥራት እድላቸውን በእጅጉ ሲጨምር ለሌሎች ደግሞ እምብዛም ተጠቃሚ አያደርግም። በጣም ትኩረታችንን የሳበው ነገር የስልጠናው ውጤት በተቀባዩ እና በስደተኛው ማኅበረሰብ መካከል በጣም የተለያየ መሆኑ ነው። ውጤቱ እንደሚያመለክተው ሥልጠናው በስደተኞች ላይ በጎ ተጽእኖ እንዳለው ሲያመላክት፣ በአስተናጋጁ ማኅበረሰብ አባላት ላይ ግን ተጽእኖው አሉታዊ ነው። ምስል 2 በአማካይ እንደሚያሳየው፣ የስልጠናው ተሳታፊዎች ፤ ተሳታፊ ካልሆኑት ጋር ሲነፃፀሩ፣ ስደተኞ ሰልጣኞች ከስልጠናው በኋላ (በተለይ መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ) ስራ የማግኘት እድላቸው ከፍ ያለ ሲሆን በአንፃሩ፣ ከንጽጽር ቡድናቸው ጋር ሲታይ፣ የተቀባዩ ማህበረሰብ ተሳታፊዎች ስራ የማግኘት እድላቸው ዝቅተኛ ነው (በተለይ በመደበኛው ዘርፍ)። ፕሮግራሙ በተቀባዩ ማኅበረሰብ አባላት ላይ ያለው አስገራሚ አሉታዊ ተጽእኖ ወደ ሥልጠናው ዘርፍ መርጠው በገቡ

ሰዎች ማንነት በከፊል ሊገለጽ ይችላል። የስልጠናው የተሳተፉት እና ያልተሳተፉት (የንጽጽር ቡድኑ) በመሠረታዊ አወቃቀር ተመሳሳይ ቢመስሉም፣ የተቀባዩ ማህበረሰብ አባላት ቀደም ሲል ያገኙት ከነበረው ገቢ አንፃር በእጅጉ ይለያያሉ። ይህ የንጽጽር ቡድኑን ቀድሞ የነበረ ጠንካራ የሥራ ገበያ ትስስር ሊያመለክት ይችላል። ውጤቱ እንደሚያመለክተው ስልጠናው ፤ ከገቢ አንጻር ፤ እነዚህን ቀደምት ልዩነቶች ለማካካስ አለመቻሉን ነው።

## ምስል 2፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥራ ለማግኘት ያለው ተጽእኖ




ማስታወሻዎች፡ የዳግም ግምት፣ ስታንዳርድ ኤረር በግለሰብ ደረጃ፣ N=1,650 (አስተናጋጅ=775፣ ስደተኛ=875)
ምንጭ፡ አጠኚዎቹ

ምስል 2 ደግሞ ወንዶች በከፍተኛ ደረጃ ሥራ የማግኘት እድላቸው ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል። በእርግጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተሳትፎ ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች የሥራ እድል በማስፋት የበለጠ ውጤታማ ነው። ቀደም ሲል የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከፆታ ጋር በተገናኘ የሚኖረው የተጽእኖ ልዩነት በከፊል በሙያ ምርጫ ልዩነት ሊገለጽ ይችላል (Kruppe & Lang, 2018)። ከዚህ ጋር ተያይዞ ወንዶችና ሴቶች ራሳቸው የሚመርጡት የቴክኒክና ሙያ ስልጠና የሙያ ዘርፍ የተለያየ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ።

ስልጠናዎቹ የሚያተኩሩባቸው በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ላይ ተጨማሪ ትኩረት የሚሰቡ የተለያዩ የተፅዕኖዎች ውጤቶች አሉ። የቤት አያያዝ እና የብየዳ ፕሮግራሞች ተመራቂዎች ፕሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ በኋላ ሥራ የማግኘት እድላቸው ከፍ ያለ ሲሆን፣ በመታጠቢያ ቤት  እቃዎች ገጠማ እና በኤሌክትሪክ ተከላ ክፍሎች ውስጥ ለሚመረቁ ተመራቂዎች ግን ይህ አይነት የስራ እድል የለም። ከዚህ ጋር ተያይዞም ስልጠናው ለስደተኞች የበለጠ የተሳካ ሲሆን ይህም በከፊል ስደተኞቹ በብዛት የቤት አያያዝ እና የብየዳ ሙያዎችን ከመምረጣቸው ጋር ሊገናኝ ይችላል። ወንዶች ብዙውን ጊዜ ሥራ የማግኘት ዕድላቸው ሰፊ ሲሆን ፤ ያለፈው የትምህርት ደረጃ ሥራ ለማግኘት ወሳኝ ሚና እንደማይጫወትም እናስተውላለን።

የፕሮግራሙ ተሳትፎ ለተቀባዩ ማህበረሰብ አባላት እንዲሁም ለስደተኞች መደበኛ ያልሆነ የስራ እድልን በእጅጉ እንደሚጨምር ልብ ሊባል ይገባል። ይህ ግኝት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና

ሥልጠና ሥልጠናው በቤት ውስጥ አያያዝ ውስጥ ለሚሳተፉ ሰዎች ከሚያስገኘው አወንታዊ ውጤት ጋር የሚስማማ ነው (የቤት ውስጥ አያያዝ ሥራ ብዙውን ጊዜ መደበኛ ባልሆነ መንገድ ይከናወናል)።

በአጠቃላይ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም በስደተኞች ወይም በስደተኛ ተቀባይ ተሳታፊዎች ገቢ ላይ የሚያመጣውን ጉልህ ተፅዕኖ አላገኘንም።

ነገር ግን ስለወደፊቱ ተስፋ ጋር የተያያዙ ብሩህ እና ተስፋ ሰጪ የወደፊት አመላካቾች አሉ። ለምሳሌ፣ ከስልጠና ተሳታፊዎች ጋር ሲነጻጸር፣ ሁለቱም የተሳታፊ ቡድኖች (ስደተኞችም ተቀባዩም) "ከሁለት ዓመት በፊት ከነበረው ጋር ሲነጻጸር፣ የስራ እድልዎ ተሻሽሏል ትላላችሁ?" እና "የእርስዎ የግል ገቢ በሚቀጥሉት ስድስት ወራት/ሶስት ዓመታት ውስጥ እንዴት እንዲያድግ ይጠብቃሉ?" ለሚሉ ጥያቄዎች በጣም የተሻለ አወንታዊ ምላሽ አላቸው። እንደ ዋቢ መጻህፍት እና ተዛማጅ ጽሑፎች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ብዙ ጊዜ በረዥም ጊዜ የሚመጣ ውጤት እንጂ በአጭር ጊዜ የሚመጣ ፈጣን የሥራ ገበያ ውጤት እንደሌላቸው ያሳያል፡፡ ይህ አይነት የውጤት ተስፋ ለወደፊቱ በሂደት ለውጥ እንዲመጣ ጥሩ መነሻ ሊሆን ይችላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ ባለን የመረጃ ውስንነት፣ አንዳንድ አሃዛዊ እና አይነታዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የቅጥር ውጤቱ በረጅም ጊዜ ውስጥ የበለጠ አዎንታዊ ሊሆን ይችላል የሚለውን አመለካከት ነው።

በአጠቃላይ፣ በዚህ ዙሪያ ያለው የተፅዕኖ ግምገማ ውጤት ከሚጠበቀው በታች ሊሆን ይችላል፡፡ ማለትም ከስደተኛው ማህበረሰብ ለሚመጡ ተሳታፊዎች የሥራ ቅጥር ውጤቱ አዎንታዊ ሲሆን፣ የተቀባዩ አገር ተሳታፊዎች ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ተጠቃሚ ለመሆን ይቸገራሉ። በተጨማሪም፣ ምንም ዓይነት የገቢ ውጤት አልተገኘም።


የስልጠናው ተሳታፊዎች የስልጠና ዘርፍ ወይም ጾታ በተገኘው ውጤት ላይ ሚና ያላቸው መሆኑ የፕሮግራሙን ተጨባጭ ውጤት የሚገድቡ መዋቅራዊ ሁኔታዎች ትኩረት እንደሚገባቸው ያሳያል። በኢትዮጵያ ያለው ከፍተኛ የሥራ አጥነት መጠን እና የመደበኛ ሥራ ዕድል ውስንነት፤ ምንም አይነት ተጨማሪ ሥልጠና ቢወሰድም፤ ወደ ሥራ ገበያ የመግባት ዕድል ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው።

## በአካታች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም የማህበራዊ ትስስር ተፅእኖን መገምገም

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መርሃግብር ውጤታማነት ውስጥ "አካታችነት" ንድፍ አዲስ ግኝት ነው። የጋራ ስልጠናውን ለተቀባዩ እና ለስደተኛ ማህበረሰብ አባላት መስጠት ግልፅ አላማው በሁለቱም ቡድኖች መካከል ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት ማሻሻል ነው። በቡድኖች መካከል መስተጋብርን መጨመር አንዱ ለአንዱ ያለውን አመለካከት እና ባህሪ እንደሚያሻሽል ጥናቶች ይገልጻሉ(e.g., Wagner, Christ, Pettigrew, Stellmacher, & Wolf, 2006)፡፡ የዚህ ጥናት አጠቃላይ ወጤቱም አካታች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብር በብዙ ማህበራዊ ትስስር ገጽታዎች ላይ ያለውን አዎንታዊ ተጽእኖ ያሳያል።

በዚህ ጥናት (Leininger et al. (2021) የቀረበውን ሶስት የተለያዩ ባህሪያትን ማለትም እምነት፣ አካታች ማንነት እና ለጋራ ጥቅም መተባበርን የሚያካትተውን ወደላይ (Vertical) እና ወደጎን (Horizontal) አቅጣጫ የሚያሳየውን የማህበራዊ ትስስር ጽንሰ-ሀሳብ እንተገብራለን። በተለይም ወደጎን አቅጣጫ (ማለትም በቡድኖች መካከል ያሉ ትስስሮች ላይ) አዎንታዊ ውጤት አግኝተናል፡፡ በስልጠናው ካልተሳተፉት ጋር ሲነጻጸር፣ ስደተኞች እና የአስተናጋጅ ተሳታፊዎች በርቀት ለሚያውቋቸው ሰዎች በከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን እምነት ሲያሳዩ፣ ከሌሎች ጋር በተደጋጋሚ ለጋራ ጥቅም (ማለትም በማህበረሰብ ስብሰባዎች ላይ መገኘት/መደራጀት ወይም በጎ ፈቃደኝነት) የመተባበር ዝንባሌ አላቸው። ለስደተኛ ተሳታፊዎች፣ ከንጽጽር ቡድናቸው (ተሳታፊ ካልሆኑት) ጋር ሲነጻጸሩ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ጠንካራ ልዩነት ሲያሳዩ አግኝተናል። ወደላይ አቅጣጫ፣ ለእምነት ጉልህ የሆኑ ውጤቶችን ብቻ እናገኛለን። እዚህ ላይ ስደተኞች እና የአስተናጋጅ አገር ተሳታፊዎች ተሳታፊ ካልሆኑት የበለጠ የመንግስት ተቋማትን ያምናሉ። ከእነዚህ ተጽእኖዎች ውስጥ አንዳንዶቹ በጊዜ ሂደት የሚጠፉ ቢመስሉም (ለምሳሌ በማያውቋቸው ሰዎች ላይ መተማመን) ሌሎች ደግሞ በጊዜ ሂደት የሚጸና ይመስላል (እንደ የጎንዮሽ ትብብር)።

## ምስል 3 ፡ - የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና በማህበራዊ ትስስር ላይ ያለው አስተዋጽዖ




*ማስታወሻዎች፡ የFE ግምት ከንጽጽር ጋር (የጋብቻ ሁኔታ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ሃይማኖት)፣ SE በግለሰብ ደረጃ የተሰበሰበ፣ N=1,970 (አስተናጋጅ=933; ስደተኛ=1,037)*

*ምንጭ፡ አጠኚዎቹ*

አይነታዊ ማስረጃዎቻችን እነዚህን ውጤቶች የሚደግፉ እና ውጤቶቹ እውን እንዲሆኑ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን ይጠቁማሉ። ስደተኞቹ እና የአስተናጋጅ አገር ተማሪዎች የጋራ ትምህርቶቹ አስደሳች እና በስደተኞች እና በአስተናጋጆች መካከል አወንታዊ ግንኙነቶችን ለማፍራት ጠቃሚ ሆነው አግኝተዋቸዋል። የትምህርት እና ሥልጠና ክፍሎችን መጋራት በተደጋጋሚ እንዲገናኙ እና ከሥልጠናው ጊዜ በኋላም ወዳጅነት እንዲፈጥሩ አስችሏቸዋል።

በተጨማሪም፣ ስደተኞች በነፃነት መንቀሳቀስ መቻላቸው እና በዚህም ከአስተናጋጁ ማህበረሰብ ጋር በህዝብ እና በግል ቦታዎች መገናኘታቸው እንዲሁም በጋራ የማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች ላይ ማሳተፋቸው ለማሕበራዊ ትስስር መጠናከር አስፈላጊ ነው። ከተማ ባለው ሁኔታ በአዲስ አበባ ፣ ከተሳታፊዎች መካከል በርካቶች ከሌላው ቡድን አባላት ጋር ቀደም ብለው ተገናኝተዋል አልፎ ተርፎም ጓደኝነት ነበራቸው። ስልጠናው እነዚያን ግንኙነቶች ጥልቅ አድርጎታል። በካምፕ አውዶች (እንደ አሶሳ ያሉ) ይህ መስተጋብር የተገደበ ሲሆን የጋራ ፕሮግራሙ ብዙውን ጊዜ ለስደተኞች እና አስተናጋጆች ትርጉም ያለው መስተጋብር ለመፍጠር የመጀመሪያው እድል ነበር። ነገር ግን፣ ቋንቋ በከፊል እንቅፋት ነበር።

ችግር ሊሆን የሚችለው እና አንዳንዴም አስጨናቂ የሚሆነው የስደተኛ ተሳታፊዎች የብድር፣ የፈቃድ ወይም የመሬት አቅርቦት ላይ በአስተናጋጆች ላይ ያላቸው ጥገኝነት ነው። ስደተኞች ያለስራ ፈቃድ ንግድ ለመጀመር ያላቸው ብቸኛው አማራጭ የኢትዮጵያውያን ጓደኞቻቸውን (ወይም የንግድ አጋሮታቸውን) ፍቃድ በኪራይ መጠቀም ነው። ስደተኞች በአካባቢያቸው ባሉ ወገኖቻቸው ላይ ከፍተኛ ጥገኛ ሲሆኑ ኢትዮጵያዊ አጋሮቻቸው ከሸርከና በመውጣታቸው ምክንያት ስደተኞቹ የንግድ ስራዎቻቸውን ያጡባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ።

## ማጠቃለያ እና ፖሊሲ አንድምታዎች

በተለያዩ የደቡባዊ የአለም አገሮች ከፍተኛ የሥራ አጥነት ሁኔታ፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች በዓለም አቀፍ እና በአገር አቀፍ ተዋናዮች የሚተገበሩ ተወዳጅ ፕሮግራሞች ሆነው

ቀጥለዋል። በእነዚህ አገሮች ውስጥ የረጅም ጊዜ የመፈናቀል ሁኔታዎች መጨመር እና የስደተኞችን ዘላቂ ውህደት ለመፍጠር ያለ ዓላማ ለእነዚህ ፕሮግራሞች የበለጠ ትኩረት እንዲሰጥ አድርጓል። ሆኖም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በተሳታፊዎቹ የሥራ ዕድል ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ የሚደግፉ ስልታዊ ተጨባጭ ማስረጃዎች ግን ወጥነት የላቸውም። በተመሳሳይ፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አስፈላጊነት ዙሪያ በውይይት ውቅት ጎልተው ለሚታዩ ማኅበረሰባዊ ተፅእኖዎች ስንመጣ ማስረጃዎች በጣም አናሳ ናቸው።

በአጠቃላይ የእኛ ትንታኔ እንደሚያመለክተው ከንጽጽር ቡድኖች ጋር ሲታይ አጠቃላይ እንቅስቃሴዎቹ በተሳታፊዎች በጣም አዎንታዊ ግምገማ ሲደረግባቸው ፕሮግራሙ በስራ እና በገቢ ላይ ተፅእኖ እንዳለው የሚያሳዩ መረጃዎች ግን ውሱን ናቸው። በተለይም በጎንዮሽ አቅጣጫ በማህበራዊ ትስስር ውጤቶች ላይ ጠንካራ ማስረጃዎች ተገኝተዋል።

በአጠቃላይ የእኛ ትንታኔ እንደሚያመለክተው ከንጽጽር ቡድኖች ጋር ሲነፃፀሩ አጠቃላይ እንቅስቃሴዎቹ በተሳታፊዎች በጣም አዎንታዊ ግምገማ ሲደረግባቸው ፕሮግራሙ በስራ እና በገቢ ላይ ተፅእኖ እንዳለው የሚያሳዩ መረጃዎች ግን ውሱን ናቸው። በተለይም በጎንዮሽ አቅጣጫ በማህበራዊ ትስስር ውጤቶች ላይ ጠንካራ ማስረጃዎች ተገኝተዋል።

በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ መደበኛ የስራ እድሎች በጣም ውስን ሲሆኑ የተሻሻሉ ክህሎቶች እንኳን ስራ የማግኘት እድሎችን በእጅጉ የሚጨምሩ አይመስሉም። ስደተኞች የስራ ፈቃድ ባለማግኘታቸው ምክንያት ወደ መደበኛው የስራ ገበያ ለመግባት በጣም የተገደቡ ናቸው። ሆኖም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መሳተፋቸው መደበኛ ያልሆነ ሥራ የማግኘት ዕድላቸውን ጨምሮታል።

## ሣጥን 2፡ ለፕሮግራም ተፅእኖ የሕግ ሁኔታዎች አስፈላጊነት ገላጭ ምሳሌ

የስደተኞችን የመሥራት መብት የሚወስንበት መመሪያ (መመሪያ ቁጥር 02/2019) ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስኬት የሕግ ከባቢን አስፈላጊነት እና መዋቅራዊ ሁኔታዎችን ለማሳየት እንደ ምሳሌ ሊያገለግል ይችላል። በዚህ መመሪያ መሰረት አንድ ኢትዮጵያዊ የትዳር ጓደኛ ወይም ልጆች ያሉት ስደተኛ በግል ስራ ለመስራት ወይም ከተቀባይ ማህበረሰቦች አባላት ጋር በጋራ ለመስራት የመኖሪያ ፈቃድ ላያስፈልገው ይችላል። ያገቡ ስደተኛ ወንዶች ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም (ከተሻሻለ ገቢ አንፃር) ከጋብቻ ውጪ ካሉ ስደተኞች የበለጠ ተጠቃሚ ሆነው አግኝተናቸዋል።

በማህበራዊ ትስስር ረገድ የአካታች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም የሚያስገኘው ውጤት አበረታች ነው። በተለይ እምነት እና ለጋራ ጥቅም መተባበር በስልጠና ተሳትፎ አዎንታዊ ተጽእኖ ተደርጎባቸዋል፡፡ የሥራ ገበያ ተደራሽነት እና በቡድኖች መካከል ያለው ከፍተኛ የሥራ ፉክክር በጣም ፈታኝ እና አስጨናቂ አካባቢ ሊሆን ስለሚችል፣ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥም ቢሆን በጋራ መማር እና ልምድ መለዋወጥ በአዎንታዊ መልኩ ወደ ተሻለ ማህበራዊ ትስስር የሚያሸጋግር ትስስር መፍጠር መቻሉ የሚያበረታታ ነው። ውጤቶቹ በተጨማሪም የትኞቹ የማህበራዊ ትስስር አካላት ውጤታማ በሆነ መልኩ በአካታች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መርሃ ግብር ሊነኩ እንደሚችሉ የሚጠቁሙ ሲሆን ይህም የተሻለ ስልታዊ እቅድ ማውጣትና መለየትን እንዲሁም ምክንያታዊ ግብ ማውጣትን ያስችላል።

የማህበራዊ ትስስር ተፅእኖ (በስራ ስምሪት ረገድ ያለው ውጤታማነት ምንም ይሁን ምን) ጠንካራ ሆኖ የሚታይ ይመስላል፣ ይህም አበረታች ቢሆንም የውጤታማነት ጥያቄን ይከፍታል፡፡ ማለትም ማህበራዊ ትስስርን በማጎልበት ላይ ብቻ ያተኮሩ እርምጃዎች የበለጠ ወጪ ቆጣቢ አይሆኑም ነበር ወይ የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በማህበራዊ ትስስር ዘርፍ አካታች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቶች ሊጫወቱት የሚችሉ ሚናዎች እንዳሉ ውጤቶቹ ይጠቁማሉ። ሆኖም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቀዳሚ ግብ የሥራ እድልን ማሳደግና ምርታማነት መጨመር ነው። ይህ ውጤት ባልተገኘበት ሁኔታ ግን ምናልባት በተለየ መንገድ ሊደረስበት በሚችል የማህበራዊ ትስስር ተፅእኖ ላይ ተመስርቶ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን አስፈላጊነት መከላከል አስቸጋሪ ይመስላል።

በዚህ መስክ ለሚንቀሳቀሱ አለም አቀፍ እና ሀገራዊ የልማት ተዋናዮች የሚከተሉትን ዋና የፖሊሲ አንድምታዎች እና ጥቆማዎችን እናቀርባለን።

- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እንደታሰበው እንዲሠራ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች ስብስብ ያስፈልጋል። ከሁኔታዎች እና ከሥራ ገበያው ፍላጎት ጋር በጥንቃቄ መላመድ አስፈላጊ ነው። ተመራቂዎች ላይ በማተኮር፣ ሥርዓተ ትምህርትን እና የመማሪያ ቴክኒኮችን በመወሰን በማቀድ ብዙ መሥራት ይቻላል። እዚህ ላይ፣ አቅም ያላቸው ቀጣሪዎች በጣም ጠቃሚ ሊሆኑ ስለሚችሉ የቅርብ ትብብር ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞችን በቀላሉ ለማከናወን የማይቻል የሚያደርጉ እንደ መደበኛ የሥራ ገበያ የመቀበል አቅም እና የሕግ መሰናክሎች ያሉ መዋቅራዊ ሁኔታዎች አሉ። እነዚህ ሁኔታዎች በቅርበት መከታተል ወሳኝ ጉዳይ ነው ምክንያቱም የስልጠናተሳታፊዎችን ጥገኝነት ወይም ልዩ እንክብካቤ ሊፈጥሩ ስለሚችሉ እና የፕሮግራሞችን ተፅእኖ ሊያዳክሙ አልፎ ተርፎም ወደማይፈለጉ አሉታዊ ተፅእኖዎች ሊመሩ ይችላሉ፡፡ (ለምሳሌ በጥገኝነት ምክንያት በቡድኖች መካከል ያለውን ማህበራዊ ትስስር መጉዳት አይነት ያሉ) ።
- ስደተኞች በአገር ውስጥ የሥራ ገበያ (በደሞዝ ወይም በግል ቅጥር) ተሳታፊ እንዲሆኑ  ሕጋዊ መሠረትን ለማሻሻል የሚደረጉ ጥረቶች ሊጠናከሩ ይገባል። ይህ ከሥራ ፈቃዶች እና ከንግድ ፈቃዶች ጋር የተገናኙ ሂደቶችን እንዲሁም የብድር ማግኛ መንገዶች ላይ መስራትን ያካትታል፡፡ በዋናነት ለእነዚህ መሰናክሎች በመንግስት ደረጃ ቀጣይነት ያለው ውይይት እና ድጋፍ አስፈላጊነት ላይ ትኩረት ይፈልጋል። ከዚሁ ጎን ለጎን እነዚህን መዋቅራዊ ውሱንነቶች ከኮሌጁ አስተዳደር፣ ከስልጠና ተሳታፊዎች፣ ከገንዘብ አቅራቢዎች እና ከአካባቢ መስተዳደሮች ጋር በመሆን ከእውነታው የራቁ ተስፋዎችን ለመከላከል በግልፅ መወያየት ያስፈልጋል።
- ከማጣጣም ጋር በተገናኘ በመለኪያ ንድፍ ላይ ማተኮርን ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው። ፕሮግራሞች የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑት ከተሳታፊዎች ፍላጎቶች እና ተግዳሮቶች ጋር ተናበው ሲዘጋጁ ነው። ለምሳሌ ሴት ተሳታፊዎች ከአጠቃላይ የሥልጠናው ፕሮግራም ምንም ጥቅም የሚያገኙ ስለማይመስል  ልዩ ድጋፍ እና እርምጃዎች ያስፈልጋቸዋል።
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በቡድኖች መካከል ያለውን ማህበራዊ ትስስር ለማሻሻል ይረዳል። እንደ እውነቱ ከሆነ አዎንታዊ ተጽእኖ በበርካታ የማህበራዊ ትስስር ጉዳዮች ላይ የተፈጠረ ይመስላል። ይሁንና ግቡን ለማሳካት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በጣም ቀልጣፋ መሣሪያ ለመሆኑ ግልጽ ጥያቄ አለ። ይህንን ውጤት መጠቀም እና ማሳደግ አስፈላጊ ነው፣ ነገር ግን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዋና ግቡ (የሥራ ዕድል መፍጠር) ካልተሳካ ማኅበራዊ ትስስርን ማሳደግ እንደ ዋና አላማ ሊሆን አይችልም።
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጠንከር ያለ ምልከታ፣ ከሁኔታዎች ጋር ማገናዘብን እና ክትትል ያስፈልጋቸዋል። ከዚህ አንጻር የሀብት እጥረት ፕሮጀክቶቹን በቅርበት እና በፍጥነት የማላመድ አቅምን የሚቀንስ ከሆነ ፕሮግራሙን ማሳደግ ችግር ይኖርበታል። ለምሳሌ፣ የስራ ፍላጎት፣ የገበያ ተለዋዋጭነት እና የስደተኞች የውህደት ጥረቶች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ የፖለቲካ ምህዳሮች በፍጥነት ስለሚለዋወጡ ከከተማ፣ ከከፊል-ከተማ እና ከገጠር አካባቢዎች አንድ ጋር ሊነፃፀሩ አይችሉም። እንዲሁም የተመራቂዎች መገለጫ (ማለትም፣ የኑሮ ሁኔታ፣ የቋንቋ ችሎታዎች) በስፊው ስለሚለያይ ስርዓተ ትምህርቱንም ሆነ የማህበራዊ ትስስር ዘዴዎች እና እርምጃዎችን ይህንን መሠረት አድርጎ መቃኘት ያስፈልጋል።
- በዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ አገሮች ውስጥ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ከመካከለኛ እስከ የረዥም ጊዜ ተጽእኖዎች ላይ ያለውን የተገኘ እውቀት ማሳደግ ወሳኝ ነው። ከዚህ ቀደም የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የስራ ገበያው ተፅእኖ ጊዜ የሚወስድ እና ከበርካታ አመታት በኋላ የሚታወቅ ነው። በተለይ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ማኅበረሰባዊ ተፅእኖ በሚመለከት ብዙ ጥናት ሳይደረግበት በመቆየቱ የማስረጃ መሰረቱ መስፋት ይኖርበታል።

# ዋቢዎች

Brown, A., Mackie, P., Dickenson, K., & Gebre-Egziabher, T. (2020). *Urban refugee economies: Addis Ababa, Ethiopia*. London: International Institute for Environment and Development.

Card, D., Kluve, J., & Weber, A. (2010). Active labour market policy evaluations: A meta-analysis. *Economic Journal, 120*(548), 452-477.

Funk, E., Groß, L., Leininger, J., & von Schiller, A. (2018). *Lessons learnt from impact-oriented accompanying research: Potentials and limitations to rigorously assessing the impact of governance programmes* (Discussion Paper 28/2018). Bonn: German Development Institute / Deutsches Institut für Entwicklungspolitik (DIE).

Kluve, J., Puerto, S., Robalino, D., Romero, J. M., Rother, F., Stöterau, J. ... Witte, M. (2019). Do youth employment programs improve labor market outcomes? A quantitative review. *World Development, 114*, 237-253.

Kruppe, T., & Lang, J. (2018). Labour market effects of retraining for the unemployed: The role of occupations. *Applied Economics, 50*(14), 1578-1600.

Leininger, J., Burchi, F., Fiedler, C., Mross, K., Nowack, D., von Schiller, A., Sommer, C., Strupat, C. & Ziaja, S. (2021). *Social cohesion: A new definition and a proposal for its measurement in Africa* (Discussion Paper 31/2021). Bonn: DIE.

Paluck, E. L., Green, S. A., & Green, D. P. (2019). The contact hypothesis re-evaluated. *Behavioural Public Policy, 3*(2), 129-158.

Stöterau, J., Kemper, J., & Ghisletta, A. (2022). *The impact of vocational training interventions on youth labor market outcomes: A meta-analysis.* Retrieved from http://dx.doi.org/10.2139/ssrn.4217580

UNHCR. (2023a). *Refugee data finder*. Retrieved from https://www.unhcr.org/refugee-statistics

UNHCR. (2023b). *Operational Data Portal. Total refugees and asylum seekers*. Accessed 16 October 2023. Retrieved from https://data2.unhcr.org/en/country/eth

Wagner, U., Christ, O., Pettigrew, T., Stellmacher, J., & Wolf, C. (2006). Prejudice and minority proportion: Contact instead of threat effects. *Social Psychology Quarterly, 69*(4), 380-390.

World Bank. (2012). *World Development Report 2013: Jobs*. Washington, DC: Author. Retrieved from http://hdl.handle.net/10986/11843

World Bank, UNESCO, & ILO. (2023). *Building better formal TVET systems: Principles and practice in low- and middle-income countries*. Washington D.C., Paris, Geneva: Authors.

**አቢስ ጌታቸው** በኢሰርቭ ኮንሰልትስ ኢትዮጵያ የስደተኞች እና የተፈናቃዮች ጥናት ክፍል ተመራማሪ ናቸው።
ኢ-ሜል: abis.getachew@ethsurv.com

**ዶ / ር ሊዛ ሆክል** በRWI - Leibniz Institute for Economic Research in the research group "Migration and Integration".የምርምር ቡድን ውስጥ ተመራማሪ ናቸው።
ኢ-ሜል: lisasofie.hoeckel@rwi-essen.de

**ዶ / ር ያና ኩንት** German Institute of Development and Sustainability (IDOS) በ"የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ" (Transformation of Political (Dis-)order) ጥናት ፕሮግራም ከፍተኛ ተመራማሪ ናቸው።
ኢ-ሜል: jana.kuhnt@idos-research.de

**አብዲራህማን ሙሁመድ** በጅጅጋ ዩኒቨርሲቲ የፍልሰት ጥናት ተቋም (IMS) የሶሺዮሎጂ ረዳት ፕሮፌሰር እና ተመራማሪ ሆነው ሰርተዋል። በአሁኑ ጊዜ በሩህር-ዩኒቨርስቲ ቦኩም (RUB) የዶክትሬት ዲግሪያቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ።
ኢ-ሜል: abdiraxmaan6@gmail.com

**አርሚን ቮን ሺለር (ፒኤችዲ)** German Institute of Development and Sustainability (IDOS) "የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ" (Transformation of Political (Dis-)order) ጥናት ፕሮግራም ከፍተኛ ተመራማሪ ናቸው።
ኢ-ሜል: armin.schiller@idos-research.de

ምስጋና

በጀርመን ፌዴራል ኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ሚኒስቴር (BMZ) ተልዕኮ እና በኖርዌይ የልማት ኤጀንሲ (NORAD) በጋራ ፋይናንስ የሚደረገውን የGIZ - QEP ፕሮግራም በዚህ ጥናት ከእኛ ጋር በትብብር ለመስራት ስለወሰኑ እናመሰግናለን። በዚህ ትብብር ውስጥ ለነበራቸው ግልጽነት እና ጥልቅ ፍላጎት እናመሰግናለን።

*This publication is funded by the German Federal Ministry for Economic Cooperation and Development (BMZ) and supported by the Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) GmbH.*

Suggested citation:
Getachew, A., Höckel, L., Kuhnt, J., Muhumad, A.A., & von Schiller, A. (2023). *Improving employment and social cohesion among refugee and host communities through TVET: Evidence from an impact assessment in Ethiopia* (IDOS Policy Brief 27/2023). Bonn: IDOS. https://doi.org/10.23661/ipb27.2023

ማሳሰቢያ:
በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተገለጹት አመለካከቶች የጸሐፊዎችን እንጂ የIDOS አመለካከቶችን ወይም ፖሊሲዎችን የሚያንፀባርቁ አይደሉም።.

Except otherwise noted, this publication is licensed under Creative Commons Attribution (CC BY 4.0). You are free to copy, communicate and adapt this work, as long as you attribute the German Institute of Development and Sustainability (IDOS) gGmbH and the author(s).

IDOS Policy Brief / German Institute of Development and Sustainability (IDOS) gGmbH

ISSN (Print) 2751-4455
ISSN (Online) 2751-4463

https://doi.org/10.23661/ipb27.2023

© German Institute of Development and Sustainability (IDOS) gGmbH
Tulpenfeld 6, 53113 Bonn
Email: publications@idos-research.de
https://www.idos-research.de

Printed on eco-friendly, certified paper.